# መቅደላ

የዐማራ ኅልውና ለኢትዮጵያ አንድነት ድርጅት (ዐኅኢአድ) ልሣን

የዐማራ ኅልውና መጠበቅ፣ ለኢትዮጵያ አንድነት መጠበቅ ዋስትና ነው!

ፈለገ አሥራት የትውልዳችን ቃል ኪዳን ነው!

ቅጽ: ፩ ቁጥር: ፩፬ ቀን: ግንቦት ፪፬

በየ15ቱ ቀን ዘወትር ኀሙስ የሚወጣ


## የጠ/ሚ ዶ/ር አብይ የቤተመንግሥት ቆይታና መሰረታዊ ችግሮች!!

ዶ/ር አብይ የኢሕአደግ ጠ/ሚኒስትርነቱን ተረከቡ ከተባለ እነሆ ሁለት ወራት እያለፋት ነውና ላለፉት 28 ረጅም ዓመታት በትግሬ-ወያኔ በኢትዮጵያ ሕዝብ ላይ ሲፈጸም የቆየዉ ሕገ ወጥ የሰቆቃና የግድያ አስተዳደርና በተለይ ደግሞ ሕገመንግሥት በሚል "ሽፋን" በዐማራ ነገድ ላይ የዘር ማፅዳትና የዘር ማጥፋት በጅምላ እየተፈፀመበት ያለ መሆኑ ይታወቃል።

ይህ ግፍ አልበቃ ያለ ይመስል በተለይ በአዲስ መልክ የተቀጣጠለዉ "የወልቃይት ጠገዴ የማንነት ጥያቄ" ተጨምሮበት ላላፉት ሦስት ዓመታት ከነበረዉ ሕዝባዊ አመጽና ይፋዊ ግድያ አኳያ እኒህ ሁለት ወራት የዶ/ር አብይ የቤተመንግሥት ቆይታ ወሳኝ ፖለቲካዊ ርምጃዎችን ለመዉሰድ አጭር ጊዜ አልነበረም።

ይሁን እንጅ ዶ/ር አብይ በነዚህ ሁለት ወራት የቤተመንግሥት ቆይታቸዉ በተለያዩ የትግሬ-ወያኔና ኦነግ ክልል በሚሏቸው መድረኮች ላይ እየተገኙ ከአካባቢ ሕዝብ ጋር ሊስማሙና ስሜት የሚኮረኩሩ ንግግሮችን ከመናገር ባለፈ እስካሁን ድረስ ወደ እዉነተኛ የለዉጥ ሂደት ለመጀመር የሚያስችሉ ርምጃዎችን ሊወስዱ ባለመቻላቸዉ የዐማራ ኅልዉና ለኢትዮጵያ አንድነት ድርጅት (ዐኅኢአድ) ከልብ እያዘነ ለዚህ ምክንያቶች ምን ሊሆኑ እንደሚችሉ የተለያዩ መላምቶችን እንደሚከተለዉ በአጭሩ ለማቅረብ ሞክሯል።

ዶ/ር አብይ የኢሕአዴግ ጠ/ሚ ሆነዉ እንደተሰየሙ የመጀመሪያዉ ይፋዊ "የጽሑፍ ንግግሩ" በብዙዎች ዘንድ የራሳቸዉ ዝግጅት ይሆናል ተብሎ ይገመት ነበርና በዚያ ንግግር የትግሬ-ወያኔ አስተዳደር የኢትዮጵያን ሥም ሲጠራ ይቅርና እጅጉን ይጸየፈዉ የነበረዉን በጥሩ አንደበትና ፈረሃ እግዚሐብርን ተላብሰዉ ስለ ኢትዮጵያና ኢትዮጵያዊነት ደጋግመዉ በኩራት በመናገራቸዉና ሌሎችንም ስሜት ኮርኳሪ አቀራረቦች አካተዉ ስለ ሰላም፣ አንድነትና እኩልነት መሰበካቸዉን ብዙዉ አድማጫ በአወንታዊ መልክ ተቀብሎቷል።

ይሁን እንጅ ያ መልካም ንግግር እንዳለ ሆኖ ጠ/ሚ ዶ/ር አብይ ከንግግር ባለፈ አንድም አዲስ የአመራሩ "ፍኖተካርታ/መርሃግብር" ይዘዉ መቅረብ አለምቻላቸዉ በግልጽ መታየቱ ደግሞ የዶ/ር አብይ ወደ ሥልጣን የመጡበትን ቅንብርና ዘዴ በግልጽ ያሳበቀበ ሁኔታ በግልፅ መታየቱ ነዉ። ምክንያቱም ዶ/ር አብይ እዉነተኛ የለዉጥ ሐዋሪያ ቢሆኑ/ወይም ለመሆን ቢፈልጉ ኖሮ ኢትዮጵያንና በትግሬ-ወያኔ እየተንገላታ ያለዉን ሕዝቧን በየትኛዉ የፖለቲካ አቅጣጫ ሊወዷቸዉ እንዳሰቡ የራሳቸዉን "ፍኖተካርታ" በዚያ ልዩና አጋጣሚ መድረክ ላይ በቆራጥነትና በግልጽ ከማቅረብ የበለጠ መልካም አጋጣሚ ጭራሽ ሊኖር አይችልምና ነበር። ለአንድ ቀን ቆይታም እንኳ ቢሆን!!

ሆኖም ግን ዶ/ር አብይ ይህን አለማድረጋቸዉ ብቻ ሳይሆን የእርሳቸዉም አመራር የትግሬ-ወያኔ የኢትዮጵያን ሕዝብ ሀብት እየዘረፈና እርቃኑን እያስቀረበት ያለዉን "የልማታዊ መንግሥትን፣ የትግሬ-ወያኔ/የኢሕአዴግ አገር በታኝና ሕዝብ ከፋፋይ የሆነዉን መርሃግብሩን የሚያስቀጥሉ መሆናቸዉን ከመናገራቸዉ ባሻገር በወንጀለኛ የትግሬ-ወያኔ ጄኔራሎች የሚመራዉ ሰራዊትና የአፈና መዋቅሩ በሰላማዊ ሕዝባችን ላይ እያደረሱ ያሉትን ግድያ፣ እስራትና ማፈናቀል እጅግ በጣም በሚያሳዝን መልኩ አሞካሽተዉና አሞግሰዉ በግልፅ ማቅረባቸዉ ዐኅኢአድ በመገረምና በሃዘን የታዘበዉ ነዉ።

ከዚህ በመነሳት በቀጥታ ሊነሳ የሚችለዉ ትልቁ ጥያቄ ዶ/ር አብይ ያን ልዩ አጋጣሚ መድረክ ለዚያ ተራ ንግግር ሊጠቀሙበት ለምን ፈለጉ? ለሚለዉ ጥያቄ በትቂቱም ቢሆን የተወሰኑ መላምቶችን ከማሳየት ባሻገር አሁንም ዋናዉና ትልቁ የሕዝባችን ጥያቄ በተለይ ደግሞ በዐማራ ነገድ ላይ እየተፈፀመ ካለዉ የዘር ፍጅት ፖሊሲ አኳያ ዶ/ር አብይ ሊከተሉት የሚገባዉን ትክክለኛ የመፍትሔ ሃሳቦች ዛሬም በድጋሜ ለማሳየት እንሞክራለን። የዚህ ጽሑፍ ዋና መነሻና መድረሻም ይሄዉ ነዉና።

እናም የዶ/ር አብይ ንግግር ስሜት ከሚኮረኩሩ ቃላት ባለፈ ለምን "ፉነተካርታ ሊኖረዉ አልቻለም" ለሚለዉ ምክንያቶችን በሚከተሉት መላምቶች ለማሳየት እንሞክራልን፡-

1. አንዱና ዋና ጉዳይ የዶ/ር አብይ ትልቁ ጥረት የኢትዮጵያ 7ኛዉ ንጉሠ ነገሥት የመሆን የቆዬ ሕልማቸዉን ለማሳካት እንጅ የኢትዮጵያ ሕዝብ በትግሬ-ወያኔና ተላላኪዎቹ አማካኝነት ላለፉት 28 ረጅም ዓመታት እየደረሰበት ያለዉን ሁለንተናዊ መሠረታዊ ችግር በቅጡ መረዳት አለመቻል፣
2. ወይም ደግሞ የፖለቲካና አገር የመምራት ክዕሎትና ግንዛቤ አለመኖር፤
3. አለያም የትግሬ-ወያኔ ባላፉት 28 ዓመታት አስከፊ አስተዳደሩ ሁሉም ነገር ለትግራይና ትግሬዎች ብቻ እያለ የሄደበት ዐይን ያወጣ ስግብግብ አካሄድ በሁሉም ኢትዮጵያዊ ዘንድ ሙሉ በሙሉ እየታወቀና እርቃኑን እየቀረ በመሆኑ ለቀጣዩ ቆይታቸዉ ደግሞ "ኢትዮጵያና ኢትዮጵያዊነት፣ አንደንትና ሰላም፣ ብልፅግና እኩልነት" የሚሉ የለበጣ ንግግሮችን ብቻ በተለያዩ መድረኮች በመግፋት ግን ደግሞ የሕዝብን መሠረታዊ የለዉጥ ጥያቄ ወደ ጎን አሽቀንጥሮ በመጣል አሁንም ያዉ የትግሬ-ወያኔ/ኢሕአዴግን የቀየ አገር የማፍረስ መርሃግብሩን ለማስቀጠል አዲሱን አቀራረብ ዶ/ር አብይን ወደ ፊት በማምጣት አዲሱ ስልት ሊሆን መቻሉ ናቸዉ።

ይህም በመሆኑ የመጀመሪያዉ ይፋዊ የጠ/ሚኒስትሩ ንግግሩ ከላይ ለማሳየት በሞከርናቸዉ መላምቶች መድረኩን በሚያማምሩ ቃላቶች የታጀቡ ግን ደግሞ ምንም ዓይነት ከበፊቱ የተለየ "ፉነተካርታ" ያልነበረዉ እንዲሆን አድርጎታል።

ከላይ ላማሳየት እንደተሞከረዉ በመጀመሪያዉ የጠ/ሚ ንግግር ላይ ተመርኩዘን ያቀረብናቸዉ መላምቶች ሲሆኑ ከዚያ በኋላ ባሉት የሥራ ቀናትና ሳምንታት የጠ/ሚኒስትሩን ከካቢኔ እስከ ሚኒስትር ዴታዎች ያለዉን አሿሿሙ ገባ ብለን ስንመረምር ደግሞ ያዉ እንደ ትላንቱ "ዉኃ ቅዳ ዉኃ መልስ" መሆኑና የትግሬ-ወያኔ ጄኔራሎች አሁንም የሠራዊቱ የበላይ አዛዦች መሆናቸዉ፣ በሕዝባችን ላይ ግድያና ግፍ እያወረደ ያለዉ የአፈና መዋቅሩ ባለበት እንዲቀጥል መደረጉና በሕገወጥ መንገድ አገሪቷን በእጅ አዙር እየገዘዛትና በሰላማዊ ዜጎች ላይ ልዩ ጥቃት እየፈጸመ ያለዉ ሕገወጡ "የአስቸኳይ ጊዜ አዋጁ" ዛሬም ድረስ እንዲቀጠል ማድረጋቸዉ ከላይ ለማሳየት ከሞከርናቸዉ መላምቶች ጋር መሳ ለመሳ የሚሄዱ ናቸዉ።

እናም ሁለተኛዉ የዶ/ር አብይ መሰረታዊ ችግር በመጀመሪያዉ ንግግራቸዉ ጊዜ የተፈጠረላቸዉን መልካም አጋጣሚ "ልቦና ገዝተዉ" ሊጠቀሙበት አለመፈለጋቸዉ ብቻ ሳንይሆን እንዲያዉም በሂደት የታየዉ "ሁለት ወርቃማ የተግባር ወራቶችን" በትግሬ-ወያኔ ካድሬዎችና ከፍተኛ ተሿሚዎች በተሞላዉ የኢሕአዴግ ጽ/ቤት ኃላፊዎች በየጊዜዉ ለንባብ ተዘጋጅቶ የሚጠብቃቸዉን ወረቅት የትግሬ-ወያኔና አነገ አጋጣሚዉን ተጠቅመዉ ወደ ሸነሸናቸዉ ክልል ተብዮዎች ይዘዉ ከመሮጥና ለሚሄዱበት አካባቢ ሕዝብ ስሜት ቆርቋሪ ንግግሮችን ከማድረግ ባለፈ ምንም ዓይነት አዲስ ፉነተካርታ/መርሃግበር ሊያቀርቡ አልቻሉም።

ይህም በድጋሜ በግልጽ የሚያሳየዉ የዶ/ር አብይን የትግሬ-ወያኔ ታማኝነትንና ተባባሪነትን እንጅ የዶ/ር አብይን ቆራጥነትና ለሕዝብ መሰረታዊ ለዉጥ ጥያቄ ተገዥነትን አይደለም። ምክንያቱም ዶ/ር አብይ ቆራጥነቱና ለሕዝብ እዉነተኛ መሰረታዊ

ለዉጥ ጥያቄ ተገዥ ቢሆኑ ኖሮ ሌላዉ ቢቀር እንኳ በእጃቸዉ ያለዉ የትግሬ-ወያኔና ኦነግ ሕገመንግሥት ብዙ ሊያሰራቸዉ እንደሚችል ራሳቸዉ በሚገባ ያዉቁታልና ነዉ።

ለዚህ ደግሞ ዶ/ር አብይን ከልጅነት ጀምሮ በሴራ ፖለቲካና በተላላኪነት ኮትኩቶ ያሳደገዉ መለስ ዜናዊ በአንድ ወቅት የካቢኔ አባል አድርጎ የሾማቸዉን ተላላኪዎች ሲሻዉ በሌላ ጊዜ አሽቀንጥሮ ከመጣል ባለፈ "ኦሕዴድ እንደ ድርጅት (መለስ) የሚሰጠዉን ትዕዛዝ የማይቀበል ከሆነ ሙሉ በሙሉ አመራሩን አስሬ አነግን ከዉጭ አመጣለሁ" እያለ ያስፈራራቸዉ እንደነበር ሁሉም የሚያዉቀዉ የአደባባይ ሚስጢር ነበር።

በመሆኑም ችግሩ ያለዉ ዶ/ር አብይ ከላይ ከተነሱት ሦስት መላምቶች ቢያንስ የአንዱ መላምት ባለቤት በመሆናቸዉ እንጅ በታሪክ አጋጣሚ ያገኙትን መድርክና ሥልጣን በመጠቅም ኢትዮጵያን ሙሉ በሙሉ የኢትዮጵያ ሕዝብ ወደ ጠየቀዉ አዲስ የሥርዓት ለዉጥ መዉሰድ የሚያስችለዉን ቁራጥ ርምጃ ከወራት በፊት በጀመሩ ነበር።

ይህን ቢያደርጉ ኖሮ ደግሞ የብዙዎችን ድርጅቶችንና የመላ ኢትዮጵያን ሕዝብ ሙሉ ድጋፍ ማግኘት ብቻ ሳሆን በኢትዮጵያ ታሪክ ዉስጥ እዉነተኛ የሕዝብ መሪ ሆነዉ ለዘላለም በታሪክ መወሳት የሚያስችል ተግባር ማከናወን ይሆንላቸዉ ነበር። ያኔም እነ ጆርጅ ዋሽንግተንና አብርሃም ሊንከን በአሜሪካ የፖለቲካ ታሪክ ልዩ ቦታ የተሰጣቸዉን ያህል ዶ/ር አብይም በትግሬ-ወይኔ አፓርታድ ሥርዓት ፍዳዉን ለሚያየዉ ለኢትዮጵያ ሕዝብ የልዉጥ ሐዋሪያና እዉነትም **"ዐብይ/ታልቁ መሪያችን"** የሚል የክብር ሥም ይሰጣቸዉ ነበር።

ለዚህ ደግሞ እንኳን ለዘመናት ለኢትዮጵያ ሉዐላዊነትና ክብር ከወንድሞቹ ጋር ደሙን ሲያፈስና አጥንቱን ሲከሰክስ ከኖረዉ ከኦሮሞ ኅብረስተሰብ ማዕፀን የመጣን ኢትዮጵያዊ ቀርቶ የኢትዮጵያ ሕዝብ ዛሬም ድረስ የየትኛዉ ጎሳ አባል ነዉ ሳይል እዉነተኛና ቁራጥ መሪዉን ምንጊዜም በደስታ ተቀብሎ ይኖር የነበር ሕዝብ መሆኑ ነዉ። አዲሱ የጎሰኝነቱ ልክፍቱ ያለዉ ያዉ በትግሬ-ወያኔዎቹና ተላላኪዎች የከፋፍለፍ ግዛና ግደል ቀመር እንጅ የኢትዮጵያ ሕዝብ አይደለም።

ሌላዉ ከላይ ስለ ኦሕዴድ ስናወሳ በፀረ-ዐማራዎች በነ በረከትና ጓደኞቹ (ሕላዊ ዮሴፍ፣ ወዘተ) የሚዘወረዉ ብአዴን የሚባለዉ ነዉረኛ ድርጅት ሙሉ በሙሉ ሎሌነቱና ጉዳይ አስፈፃሚ የትግሬ-ወያኔ መሆኑን ማንም ያዉቀዋል በሚል እንጅ ብአዴን ከኦሕዴድ የከፋ የትግሬ-ወያኔ ተላላኪ ድርጅት መሆኑን ለአፍታም ቢሆን በመርሳት አይደለም።

ከላይ ስለ ጠ/ሚ ዶ/ር አብይ የአመራር ችግሮች በማሳያነት ያነሳናቸው ግልጽ ጭብጦች ታላቅ ትኩረት በመስጠት ዐኅኢአድ ቀደም ብሎ በተለያዩ ጊዜያት በመቅደላ ልዩና መደበኛ ዕትሞች የችግሩን ስፋትና ጥልቀት ለሕዝብ ለማስጨበት እንደሞከረዉ ሁሉ አሁንም መሰረታዊዉ የሕዝብ ችግር በለበጣ ንግግሮችና ዙሪያ ጥምጥም በመዞር የሚፈታ አለመሆኑን በአንክሮ ማስገንዘብ እንፈልጋለን። ሕዝባችንም ይህን ጠንቅቆ ይገነዘባል።

ለዚህም ዋናዉ ምክንያት ላለፉት ፪፰ አመታት በዐማራ ነገድ ላይ ሕግን ሽፋን አድርጎ የታወጀዉ የዘር ማጽዳትና የዘር ማጥፋት አዋጅ እስረኛ በማስፈታት፣ የምርጫ ሕጉ ይሻሻል በማለት፣ የኢኮኖሚ ተጠቃሚነት ይኑር፤ ወዘተ በማለት ብቻ የሚፈታ አይደለም። እንዲያዉም እነዚህ ጥያቄዎች ለዐማራዉ ነገድ የቅንጦት ያህል ይቆጠራሉና የቱኑም ያህል ጆሮ አንሰጣቸዉም። እርግጥ ነዉ በብዙ ሽዎች በየእስር ቤቱና ጉድጓዶች ዉስጥ የተጣሉ የዐማራ ነገድ ተወላጆች ያሉበት አሰእቃቂ ሆኔታ ምን ያህል አስከፊ እንድሆን ለማንም ግልጽ መሆኑን በምርሳትም አይደለም።

ይሁን እንጅ ካላይ የተነሱት ጥያቄዎች በኢትዮጵያ ታሪክ ላይ የራሱን ትልቅ አወንታዊ አሻራ ያሳረፈዉና በአራቱም ማዕዘናት የአገር ድንበር በመጠበቅ ለዘመናት ደሙን ሲያፈስና አጥንቱን ሲከሰክስ የኖረዉ የዐማራ ነገድ በአገሩ በሰላም እንዳይኖር የትግሬ-ወያኔና ኦነግ ሕገመንግሥት ብለዉ ባወጡት ሰነድ (ይህን አገር ሠሪና ጠባቂ ነገድ) ሆን ብሎ በጠላትነት በመፈረጅና ከአገሩ የፖለቲካና ኤኮኖሚያዊ ሚና ለ፪፰ ዓመታት በማገድና በማግለል የዘር ማጽዳትና የዘር ማጥፋት ወንጀል እየፈጸሙበት ነዉና ጥያቄዉ በቀጥታ ሕገመንግሥታዊ ጥያቄ መሆኑ ለአፍታም ቢሆን እንኳ ቸል የምንለዉ አይደልም።

ለዚህ ደግሞ ሕገመንግሥት ተብዮዉን በወቅቱ አዘጋጀን ያሉ እንደነ ዶ/ር ነጋሶና ሌሎች ጭምር "አሁን አገሪቱ የምትመራበት ሕገመንግሥት የኢትዮጵያ ሕዝብ ያልመከረበትና ጉዳዮ የሚመለከታቸዉን ኢትዮጵያዊ አካሎች ሆን ብሎ

ያገለለ የኢሕአዴግ ሕገመንግሥት ነዉ" ብለዉ በተለያዩ መድረኮች ላይ የሚያዉቁትንና የሆነዉን አስረግጠዉ የተናገሩትና ሰንዱም በተጨባጭ የሚያሳየዉ ይህንኑ በዐማራ ነገድ ላይ የተቀነባበረ ሴራ መሆኑን ነዉ።

እናም ዶ/ር አብይ የትግሬ-ወያኔዉ ጭምብል ለሆነዉ ኢሕአዴግ ጠ/ሚ ከመሆን ባሻገር በታሪክ ኢጋጣሚ የተገኘዉን ልዩ ክስተት በመጠቀም ኢትዮጵያ ለሁሉም ዜጎች እኩል የምትበጅ አገር መሆን ወደ ሚያስችለዉ የለዉጥ መንገድ ለመሄድ ሌላ ተጨማሪ ጊዜ ሳይባክኑ አሁኑኑ ቆራጥ ርምጃ መዉሰድ ይኖርባቸዋል።

በየትኛዉም መመዘኛ በአንድ የኅበረተሰብ ክፍል ላይ ሁለንተናዊ የማጥቃት ዘመቻ ለመፈጸም ተበሎ የረቀቀን የትግሬ-ወያኔና አነግ የተሰኔ ሕገመንግሥታዊ ሰንድ ይዘዉ ስለ ሰላምና ብልጽግ፣ ዴሞክራሲና እኩልነት ማዉራት ከቶዉንም የሚቻል አይቻልምና ይህ ሕገአራዊት ሌላ ተጨማሪ ግድያ፣ ዝርፊና ማፈናቀል ሳያስከትል ሊታገድ ይገባል። በምትኩም ሁሉንም የኢትዮጵያ ሕዝብ እኩል ባሳተፈ መልኩ ለሚዘጋጅ ዴሞክራሲያዊ ሕገመንግሥት መስራት የግድ ይላል። ይህ ባልሆነበት ሁኔታ ስለ ምርጫና ሰላምና እኩልነት ማዉራት ከቶዉንም የሚታሰብ አይሆንም። የዐማራ ነገድ ተወላጆችም ይህን ሴራ እያወቁ ወደ ምርጫ ሊገቡ የሚችሉበት የፖለቲካ ምዕራፍ ሊኖር አይችልም። ይህ እንዳይሆንም ዐኅኢአድ ግልፅ አቋሙን ይዞ ይገፋል።

በመሆኑም ጠ/ሚ ዶ/ር አብይ ምንም ተጨማሪ ጊዜ ሳያባክኑ ሁሉም የፖለቲካ ድርጅቶችና ጉዳዮ የሚመለከታቸዉ የኅብረተሰብ ክፍሎች የሚሳተፉበት ሰፊና ግልፅ አገራዊ ጉባኤ የሚጠራበትን መንገድ ተግባራዊ ማድረግ ይጠበቅባቸዋል። በተናጠልና በኅን የሚደረጉ ድርድሮችና ስምምነቶች ሆን ብሎ ችግሩን ለመደባበቅና ለተመሳሳይ ችግር ሌላ ጊዜ ለመግዛት ታስቦ ካልሆነ በቀር ለግዙፉ አገራዊ ችግር መፍትሄ አጋዥ ሊሆን አይችልም።

ያለ ጥፋታቸዉ በማያዉቁት ግንቦት ፯ና አነግ አባልነት ሥም የፈጠራ ክስ ያለ አግባብ ይሰቃዩ የነበሩ ኢትዮጵያዉያን ከወያኔ እስር ቤቶች መፍታት ተገቢ ቢሆንም ለመሰረታዊዉ ችግሮች ግን መፍትሄ ተደርጎ መወሰድ አይችልም። መፍትሔዉ አንድና አንድ ብቻ ነዉ። ያም የወልቃይት ጠገዴ፣ ጠለምትና ድፍን ራያ አዘቦና አካባቢዎች እንዲሁም መተከል ላይ የትግሬ-ወያኔ በቀጥታ የፈጸመዉ ግድያና የመሬት ወረራ ያለምንም ቅድመ ሁኔታ ቆሞ መሬቶችም ወደ ሕጋዊ ባለቤቱ በአስቸኳይ መመለስና ሁሉም የኢትዮጵያ ሕዝብ በቀጥታ የሚሳተፍበት ዴሞክራሲያዊ ሕገመንግስት የሚቀረጽበትን መንገድ መከተልና ይህን ተመርኩዞ የኢትዮጵያ ሕዝብ በቀጥታ መንግሥቱን/መሪዉን ድርጅት የሚመርጠዉ መንግሥት መፍጠር እንጅ ሌላ ተጨማሪ ጊዜ ማባከን አያስፈልግም።

ይህ ታሪካዊ ሂደት እንዲሳካም ጠ/ሚ ዶ/ር አብይ የለዉጥ ሐዋሪያ ሆነዉ በመንቀሳቀስ የኢትዮጵያ ሕዝብ የሞተበትንና ሕዝባዊ አመጽ ያደረገበትን የሥርዓት ለዉጥ አገራዊ ጥያቄ ተግባራዊ ማድረግ ይጠበቅባቸዋል። ይህ ሲሆን ዐኅኢአድ ያለዉን ዕዉቀት፣ ልምድና ሰፊ ድርጅታዊ የሰዉ ኃይሉን ለዚህ ለተቀደሰ ዓላም በማስተባበር በሂደቱ ጉልህ ሚና መጫወት ይችላል። ለዚህ ተልዕኮ ተብሎ ለመነሻነት የሚያገለግል "የሽግግር ጊዜ ሰንድ" ከወራቶች በፊት በማዘጋጀት ለሕዝብ በይፋ መዘርጋቱና በተለያዩ መድረኮች ላይ ማቅረቡም በሚገባ ይታወሳል።

የዐማራ ኅልውና መጠበቅ ለኢትዮጵያ አንድነት መጠበቅ ዋስትና ነው!!

ውድ እናት ኢትዮጵያ ከቆራጥ ልጆቿ ጋር አብባ ትኖራለች!!!